# አካታች የፋይናንስ ስትራቴጂው የልማት መሠረት ነው

**ኢብሳ ነመራ** 10-09-17

በቅርቡ *ብሄራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ* የተሰኘ ሰነድ ይፋ ተደርጓል። ይህ ስትራቴጂ ባንክና የመድን ዋስትና የመሳሰሉ የገንዘብ ወይም የፋይናንስ ተቋማትን ለህዝብ ተደራሽ ማድረግን የሚመለከት ነው። ባንክና ገንዘብ የማይነጣጠሉ ናቸው። ባንኮች የቁጠባ ገንዘብን በመሰብሰብ የካፒታል ገበያ በመሆን የሚያገለግሉ ተቋማት ናቸው። በመሆኑም በአንድ ሃገር ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቅ ድርሻ አላቸው።

እንግዲህ የኢትዮጵያና የገንዘብ ትውውቅ በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን ያስቆጠረ ነው። የአክሱም ዘመነ መንግስት የሳንቲም ገንዘብ ለዚህ አስረጂነት ሊጠቀስ ይችላል። ይሁን እንጂ የገንዘብ ሥርአቱ የሃገሪቱን እድገትና ሥልጣኔ ማሽቆልቆል ተከትሎ ወደኋላ ተጉዞ የገበያ የልውውጥ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ወድቋል፤ ወደየሸቀጥ ለሸቀጥ ልውውጥ። ከዚያም እንደየአካባቢው ሁኔታ፣ በአብዛኛው ሰው የሚፈለጉ ምርቶች ሁለንተናዊ የልውውጥ ተግባርን የሚያከናውኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ገመድ፣ ቆዳ፣ አሞሌ ጨው . . . ይህን ሁለንተናዊ የልውውጥ አገልግሎት ሲሰጡ ከነበሩ ምርቶች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው። በ18ኛውና 19ኛው ክፍለ ዘመን ከአሞሌ ጨው ጋር የአውስትራሊያ *ማሪያ ትሬሳ* ገንዘብ አገልግሎት ይሰጥ ነበር። ከ1840ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ማሪያ ትሬዛ ኢትዮጵያ ውስጥ የማገልገል ህጋዊ እውቅና ተሰጠው። ከዚህ በተጨማሪ የህንድ *ሩፒና* የሜክሲኮ *ዶላር* በተለይ ለወጪና ገቢ ንግድ አገልግሎት ላይ ይውሉ እንደነበረ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

በዘመናዊ የሃገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ይፋ ገንዘብ አገልግሎት መስጠት የጀመረው በ1885 ዓ/ም በምኒልክ ዘመነ መንግስት እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ገንዘብ በ20 ቀርሺና 40 ቤሳ የተከፋፈለ ነበር። ከዚህ በኋላ በ1895 ዓ/ም የብር ሳንቲሞች ተቀረጹ። በኢትዮጵያ የባንክ አገልግሎት የጀመረው በዚህ ወቅት ነበር። በ1897 ዓ/ም በኢትዮጵያ መንግስትና ባለቤትነቱ የእንግሊዝ መንግስት በሆነው የግብጽ ብሄራዊ ባንክ መሃከል በተፈጸመ ስምመነት የአቢሲኒያ ባንክ (Bank of Abyssinia) ተመሰረተ። በዚህ ስምምነት መሰረት በኢትዮጵያ ሌላ ባንክ ማቋቋም አይቻልም ነበር። በ1898 ዓ/ም በአጼ ምኒሊክ ተመርቆ ሥራ የጀመረው አቢሲኒያ ባንክ በመጀመሪያ የኢትዮጵያን ገንዘብ አይቀበልም ነበር። ባንኩ የሚንቀሳቀሰው በአውስትራሊያ ማርያ ትሬሳ ገንዘብ ነበር። ባንኩ በሃረር፣ ድሬደዋ፣ ጎሬ፣ ደምቢዶሎና ጋምቤላ ቅርንጫፎች፣ በጅቡቲ ደግሞ የትራንዚት ጽህፈት ቤት የነበረው ቢሆንም፣ የባንኩ ተጠቃሚዎች ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ የሚኖሩ የውጭ ሃገራት ዜጎች ነበሩ። ያኔ ኢትዮጵያውያን እንኳን የባንክን ጥቅም ሊያውቁ ለተወሰኑ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ግብይቶች ካልሆነ ገንዘብም አይጠቀሙም ነበር። የዚህ ኢትዮጵያውያን የሌሉበት የአቢሲኒያ ባንክ ዋነኛ ተግባር የቁጠባ ሂሳብ መክፈት (ተቀማጭ ሂሳብ መሰብሰብ)፣ የቼክ ክፍያ መፈጸም ነበር። የኢትዮጵያ የባንክ ተደራሽነት ታሪክ በዚህ አኳኋን ኢትዮጵያውያንን ባይተዋር አድርጎ ነበር 'ሀ' ብሎ የጀመረው።

ቀዳማዊ ኃ/ ሥላሴ ወደስልጣን መምጣታቸውን ተከትሎ በ1924 ዓ/ም በግብጽ ብሄራዊ ባንክ ስር የነበረውና ለኢትዮጵያውያን ባይተዋር የነበረውን የአቢሲኒያ ባንክ ለባለድርሻዎቹ ካሳ ከፍለው እንዲዘጋ አደረጉ። በምትኩ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጲያውያን ባለቤትነት የተያዘ 750 ሺህ ፓውንድ ስተርሊንግ ካፒታል ያለው *የኢትዮጵያ ባንክ (Bank of Ethiopia)* ተቋቋም። የብሄራዊ ባንክንና የንግድ ባንክን ተግባራት አጣምሮ ያከናውን የነበረው የኢትዮጵያ ባንክ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ በድሬደዋ፣ ጎሬ፣ ደሴ፣ ደብረታቦርና ሃረር ቅርንጫፎች ነበሩት። በኢትዮጵያ ለዜጎች ተደራሽ የሆነ ባንክ እርምጃ "አንድ" ብሎ ጀመረ፣ በኢትዮጵያ ባንክ አማካኝነት።

የህም ባንክ ረጅም ጊዜ አልቆየም። በጣሊያን ወረራ ወቅት *የኢትዮጵያ ባንክ* ስራ አቆመ። በዚህ ፋንታ *ባንኮ ዲ ሮማ፣ ባንኮ ዲ ናፖሊ፣ ናዚዮናሌ ዴል ላቮሮ* የተባሉ የጣሊያን ባንኮች ቅርንጫፎች ተከፈቱ። በተለይ ባንኮ ዲ ሮማና ባንኮ ዲ ናፖሊ ዘውዳዊው ስርአት እስከከተመበት 1967 ድረስ ቀጥለው ነበር።

የጣሊያን ወረራ ሳይሳካ ቀረቶ ሃገር ለቆ ከወጣ በኋላ በ1935 ዓ/ም በ1 ሚሊየን ማሪያ ትሬዛ ዶላር *የኢትዮጵያ ባንክ* እንደገና ተመሰረተ። ይህ ባንክ እስከ 1955 ዓ/ም ድረስ የብሄራዊ ባንክና የንግድ ባንክን ተግባር ሲያከናውን ቆይቶ አሁን ወዳለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የባንኮች ሁሉ ባንክ ወደሆነው ብሄራዊ ባንክ ተከፈለ። በሌላ በኩል ከ1930ዎቹ አጋማሽ በኋላ የእርሻ ባንክ፣ የቤቶችና ቁጠባ ባንክ ወዘተ የተባሉ በተወሰነ ተግባር ላይ የሚያተኩሩ ባንኮች ተቋቁመዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ የራስዋ 1969 *የኢትዮጵያ ዶላር* በሚል ስያሜ ከዚያ በኋላ ደግሞ *ብር* በሚል ይፋዊ ስያሜ የራስዋን ገንዘብ አገልግሎት ላይ አውላለች። የአገልሎት አቅሙም እየጎለበተ ሄዷል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የግል ባንክ በ1956 ዓ/ም ነበር የተመሰረተው። ይህ የመጀመሪያ የግል ባንክ *አዲስ አበባ ባንክ* ይባል ነበር። ይህ ባንክ 51 በመቶ በኢትዮጵያውያን፣ 9 በመቶ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖሩ የውጭ ሃገራት ዜጎች፣ 40 በመቶ በለንደኑ ግሪንድሌይስ ባንክ የአክስዮን ድርሻ ነበር የተመሰረተው።

በ1966 ዓ/ም ወደስልጣን የመጣው ወታደራዊው ደርግ መንግስታዊ የእዝ ኢኮኖሚ ሥርአት ስለሚከተል ብቅ ማለት ጀምሮ የነበረውን የግል ባንክ አጠፋ። በ1968 ዓ/ም የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የግል ባንክ የነበረው አዲስ አበባ ባንክ ከጣሊያኖቹ ባንኮ ዲ ሮማና ባንኮ ዲ ናፖሊ ጋር ተቀላቅለው *አዲስ ባንክ* የተሰኘ መንግስታዊ ባንክ መሰረቱ። ከአምስት ዓመት ቆይታ በኋላ *አዲስ ባንክ* ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ተቀላቀለ። በ1976 የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንትና ቁጠባ ባንክ ከቤቶች ይዞታ ባንክ ጋር ተቀላቅሎ የቤቶች ልማትና ቁጠባ ባንክ ተመሰረተ። የግብርናና የኢንደስትሪ ልማት ባንክም እስከ 1994 ዓ/ም ባለበት እንዲቀጥል ሆነ።

እስከ 1883 ዓ/ም የአንድ ክፍለ ዘመን ያህል እድሜ የነበረው የኢትዮጵያ የባንክ እንቅስቃሴ፣ ከሌሎች ተመጣጣኝ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሃገራት ጋር እንኳን ሲነጻጸር ገና ከጅምር ያላለፈ ነበር ማለት ይቻላል። በዘወዳዊው ዘመን የነበረው ፊወዳላዊ የገባር ሥርአት የሃገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውን ግብርና እድገት አንቆ ይዞ ነበር። በአምራች ኢንደስትሪ ዘርፍ የነበረው ኢንቨስትመንትም እዚህ ግባ ሊባል የሚችል አልነበረም። አለ የሚባለውም ቢሆን በውጭ ባለሃብቶች የሚከናወን ነበር። በዚህ ኢኮኖሚያዊ ምክንያትና ህዝቡ ከባንክ ጋር ያለው ትውውቅ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ባንኮች የቁጠባ ማዕከል አልነበሩም። የባንኮቹ እንቅስቃሴም በጠቅላይ ግዛት ከተሞች፣ ምናልባት በአውራጃ ከተሞች የተገደበ ነበር። እናም የሃገሪቱ የባንክ ተደራሽነት እጅግ ኋላ ቀር ነበር።

ወታደራዊው ደርግም ብቅ ማለት ጀምሮ የነበረውንም የአምራች ኢንደስትሪና የንግድ ኢንቨስትመንት በህግ ገድቦ ነበር። እናም ቀደም ሲሉ የተፈጠሩት ለጋ ሃገር በቀል ባለሃብቶች ጠፍተው ሁሉንም ህዝብ በድህነት አስተካክሎ ነበር። የገንዘብና የባንክ እንቅስቃሴም በዚሁ ልክ አሽቆለቁሏል። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የባንኮች ቁጥር ከመቀነሱ ባሻገር የብቸኛው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንቅስቃሴ በክፍለ ሃገር ዋና ከተሞችና በአውራጃዎች የተገደበ ነበር፤ በተለይ በአዲስ አበባ። የግብርናና የኢንደስትሪ ልማት ባንክም ቢሆን በክፍለሃገር ዋና ከተሞች ብቻ የሚገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ ብድር የሚሰጠው ለመንግስታዊ ድርጅቶችና ትርፋማ መሆን ሳይችሉ ለፈራረሱ የአርሶ አደር የህብረት ሥራ ማህበራት በመሆኑ ውጤታማ አልነበረም። የቤቶችና ቁጠባ ባንክ በተለይ በአዲስ አበባና በተወሰኑ ዋና ዋና ከተሞች ለግለሰብ ቤት ሰሪዎች ብድር በመስጠት በአንጻራዊነት የተሻለ የህዝብ ተደራሽነት ነበረው ማለት ይቻላል። በአጠቃለይ ግን ህዝብና መንግስት ሩቅ ለሩቅ የሚተያዩ አንዱ ለሌላው ባይተዋር ነበሩ ማለት ይቻላል። ይህ

ሁኔታ ባንኮች የካፒታል ገበያ የመሆን አቅማቸውን አኮስምኖታል። ኮስማና የካፒታል ገበያ ደግሞ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር፣ የህዝቡን ኑሩ ማሻሻል የሚያስችሉ ኢንቨስትመንቶችን ማሳደግ አይችልም።

ከ1983 ዓ/ም ወዲህ በተለይ በባንክና በገንዘብ እንቅስቃሴ ረገድ በሃገሪቱ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ በእጅጉ የዳበረ እንቅስቃሴ ታይቷል። በአሁኑ ጊዜ በአጠቃላይ በሃገሪቱ 18 ባንኮች፣ 35 የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት፣ 18 ሺህ የቁጠባና ብድር አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። የ2009 በጀት ዓመት መረጃ እንደሚያመለክተው፣ የባንክና የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቁጠባ ሒሳብ ቁጥር 43 ነጥብ 8 ሚሊዮን ደርሷል። የባንክ ቅርንጫፎች ቁጥር 4,227 ደርሷል። የአነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት ቅርንጫፎች ቁጥር 1,748 ደርሷል። የመድን ድርጅት ቅርንጫፎች ቁጥር 492 ደረሷል።

ይህ የሃገሪቱ የፋይናንስ ተቋማትና ተደራሽነት በምን ያህል መጠን እንዳደገ ያመላክታል። በመቶ ዓመት የሃገሪቱ የባንክ (የፋይናንስ ተቋም) ታሪክ ውስጥ ባለፉ ሁለት አስርት ዓመታት የተመዘገበው እድገት እጅግ ከፍተኛና እመርታዊ ሊባል የሚችል ነው። ይሁን እንጂ በፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት ረገድ አሁንም ብዙ ይቀራል። በ2005 ዓ/ም በአለም ባንክ የተካሄደ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ መደበኛ የፋይናንስ ተቋማት ተጠቃሚ የሆኑ እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ዜጎች 22 በመቶ ብቻ ናቸው። ይህም ከሰሃራ በታች ካሉ ከኢትዮጵያ ጋር ተመጣጣኝ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ሃገራት አማካይ 34 በመቶ ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ነው። በጥናቱ ከተካተቱ መካከል 78 በመቶ ያህሉ *አነስተኛ ገንዘብ ለመበደርም ሆነ ለመቆጠብ ወደ ባንክ መሄድ አይቻልም* የሚል አመለካከት እንዳላቸው ተረጋግጧል። 12 በመቶ ያህሉ ደግሞ የፋይናንስ አገልግሎት መስጫ መዳረሻዎች ርቀት አገልግሎቱን እንዳይጠቀሙ እንዳደረጋቸው ተናግረዋል።

የኢትዮጵያን የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት ከገደቡት ምክንያቶች መሃከል የተለያዩና ተስማሚ የፋይናንስ አገልግሎት መስጫ መዳረሻዎች በበቂ ሁኔታ አለመኖር ተጠቃሽ ነው። ለምሳሌ 35 በመቶ የባንክ፣ 54 በመቶ የመድን ሰጪ ቅርንጫፎች በአዲስ አበባ የተከማቹ ናቸው። የተቀሩትም በትላልቅ የሃገሪቱ ከተሞች የሚገኙ ናቸው። የኤሌክትሪክ ሀይል መቆራረጥና የተንቀሳቃሽ ስልክ ኔትዎርክ ጥራት ማነስ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚከናወኑ የፋይናንስ ግብይቶች አስተማማኝ እንዳይሆኑ እንቅፋት መሆኑም በተጨባጭ የሚታይ ችግር ነው።

እንግዲህ ሰሞኑን ይፋ የተደረገው የብሔራዊ የፋይናንስ አካታችነት ስትራቴጂ ዓላማ ይህን ወደኋላ የቀረ የባንኮች ወይም የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት ማሻሻል ነው። *የፋይናንስ ዘርፉን ተደራሽነት በእጅጉ ያሻሽላል፣ አሠራሩንም ቀልጣፋ ያደርጋል* ተብሎ የታመነበት ይህ ስትራቴጂ፣ ሁሉን አቀፍና ዘመናዊ የሆኑ የፋይናንስ አገልግሎቶችን ተደራሽነትና ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ዓላማ አለው። ከዚህ በተጨማሪ በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጡ አመቺና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የፋይናንስ አገልግሎቶችን በፈጠራዎች በመታገዝ ለሁሉም ግለሰቦችና ድርጅቶች ተደራሽ የማድረግ ዓላማ አለው።

ስትራቴጂው *በ2012 ዓ/ም ሁሉን አቀፍና ዘመናዊ የሆኑ የፋይናንስ አገልግሎቶች ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ተረጋግጦ ማየት* የሚል ራዕይ አለው። የስትራቴጂው ተልዕኮ *የኢኮኖሚ ዕድገትን፣ ድህነት ቅነሳን፣ የፋይናንስና የገንዘብ ሥርዓት መረጋጋትን ለማገዝ በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጡ የተለያዩ፣ ተስማሚና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የፋይናንስ ምርቶችና አገልግሎቶች ፈጠራ በታከለባቸውና አመቺ በሆኑ ዘዴዎች ለሁሉም ግለሰቦችና ድርጅቶች ተደራሽ ማድረግ* የሚል ነው። ስትራቴጂው የፋይናንስ ተቋማት ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ሊሰጧቸው የሚገቡ የብድር መጠኖችን ይዘረዝራል። ይህም የፋይናንስ ተቋማት ለግል ዘርፍ ከሚሰጡት ጠቅላላ ብድር ውስጥ 15 በመቶውን ለጥቃቅን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሰጡ ያዛል። ይህ የሆነው፣ እነዚህ ዘርፎች ለኢኮኖሚ ዕድገትና ለሥራ ዕድል

ፈጠራ ከፍተኛ ድርሻ ስላላቸው ነው። በስትራቴጂው መሰረት አሁን ያለውን አድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ ለሆኑ ዜጎች የሚሰጠውን 10 በመቶ ብድር፣ ስትራቴጂው ተግባራዊ በሚሆንባቸው እስከ 2012 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ 40 በመቶ ለማደረስ ታቅዷል። የግብርናው ዘርፍ ከሃገሪቱ ጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት 38 ነጥብ 7 በመቶ፣ ከጠቅላላ የሥራ ሥምሪት ደግሞ 85 በመቶ ድርሻ አለው። ይሁን እንጂ ዘርፉ ከባንክ የሚያገኘው የብድር ድርሻ 10 ነጥብ 4 በመቶ ብቻ መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ስትራቴጂው ለግሉ ዘርፍ ከሚሰጠው ጠቅላላ የባንክ ብድር ውስጥ የግብርና ብድር ድርሻ በ2012 ዓ/ም ወደ 15 በመቶ ማደግ እንዳለበት ይገልጻል።

ስትራቴጂው የፋይናንስ ገልግሎት የሚያገኙ አድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ዜጎችን መጠንም ለማሳደግ ያቀደ ነው። በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት አገልግሎት የሚያገኙ ዜጎችን 60 በመቶ የማድረስ እንዲሁም ከፋይናንስ አገልግሎት መስጫ መዳረሻዎች በአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን ቁጥር 80 በመቶ የማድረስ ግብ አስቀምጧል። በ2012 ዓ/ም በመደበኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚቆጥቡ ዜጎችን መጠን 40 በመቶ ማድረስንም እንደግብ አስቀምጧል።

በኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት ላይ ትልቅ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳደረው የግንዛቤ እጥረት ችግር መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ። ስትራቴጂው በመሠረታዊ የባንክ ሒሳብ አከፋፈት ዙሪያ ግንዛቤ ያላቸውን ዜጎች መጠን 80 በመቶ ለማድረስ አቅዷል። በአሁኑ ጊዜ በመንግሥት፣ በግለሰቦችና በድርጅቶች የሚደረጉ ክፍያዎች በአብዛኛው የሚፈጸሙት በጥሬ ገንዘብ፣ በቼክና በክፍያ ማዘዣ ሰነዶች ነው። ስትራቴጂው ይህን ሁኔታ በመቀየር የኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ዘዴዎች ተጠቃሚ ዜጎችን 40 በመቶ የማድረስ ግብ አስቀምጧል። ይህ በሃገር አቀፍ ደረጃ የግብይት ወጪን ይቀንሳል። የሥራ ቅልጥፍናንና ውጤታማነትን ማሻሻል እንደሚያስችልም ይታመንበታል። በአጠቃላይ የተጠቀሱት የስትራቴጂው ግቦች ስኬት ቁጠባን ከማበረታታት ባሻገር ለኢንቨስትመንት አመቺ የሆነ የፋይናንስ አቅርቦት እንዲኖር ያደርጋል። የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩም ያደርጋል። ይህም ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠር የሚያስችል ሁኔታን ያደላድላል። በርካታ ዜጎች የሥራ እድል ማግኘታቸው የዜጎችን የነፍስ ወከፍ ገቢ በማሳደግ የጸረ ድህነት ትግሉን ያግዛል።